# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 73 ጥር 20 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ፉክክራችን ራሳችን ካስቀመጥነው መርህ ጋር ነው

ዋሲሁን ተስፋዬ



# ቆይታ

## < <ፋክክራችን ራሳችን ካስቀመጥነው መርህ ጋር ነው> >

ዋሲሁን ተስፋዬ

**ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ናቸው፡፡ ድርጅታቸው ኢዜማ ለምርጫ እያደረገ ያለውን ዝግጅት እንዲሁም ለምርጫው የሚሆኑ ዕጩዎችን ከማስመረጥ ጋር በተያያዘ ሲያደርገው የቆየውን እንቅስቃሴ በሚመለከት ተወያይተናል፡፡ በመቅረፀ ድምፅ ያስቀረነውን ውይይታችንን ወደ ፅሁፍ በመለወጥ ለአንባቢዎቻችን በሚከተለው መልኩ አሰናድተንዋል፡፡ መልካም ንባብ!**



*የኢዜማ የምርጫ 2013 ዝግጅት ምን ይመስላል?*

ምርጫ 2013 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ይባል እንጂ ለእኛ የመጀመሪያ ምርጫ ነው፡፡ ሀገሪቷ በታሪኳ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አድርጋ አታውቅም፡፡ ይሄ የመጀመሪያው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ይሆናል ብለን ዝግጅት እያደረግን ነው፡፡ ከፊታችን ያለው ምርጫ ብዙ ተስፋ የተጣለበት ምርጫ ነው፡፡ በሁሉም ዘርፍ ያሉ መዋቅሮቻችን በጠቅላላ ከምርጫው ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ብቻ ነው የሚሰሩት፡፡ ቀጣዩን ምርጫ እንዴት አሸናፊ ሆኖ መውጣት ይቻላል? እኛንም ሆነ ሀገርን እንዴት ያሻግራል? በሚለው ነጥብ ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን እንገኛለን፡፡

*በዕጩ ምልመላ ሂደታችሁ በሀገር አቀፍ ደረጃ እስካሁን ምን ያህል ዕጩዎችን መምረጥ ቻላቹህ?*

ሀገራችን ላይ ድርጅት ስንፈጥር ምን ዓይነት ድርጅት መፍጠር አለብን ብለን በደንብ አስበናል፡፡ በተወሰኑ ሰዎች ፍላጎት ብቻ የሚቋቋም ድርጅት ቁጥር ከመጨመር ውጪ ፋይዳ የለውም፡፡ ኢዜማ የተመሰረተው በሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ አንድ ነገር መቀየር የማይችልና አንድ አሻራ ማሳረፍ የማይችል ፓርቲ ለመሆን አይደለም፡፡ በብዙ መልኩ አዳዲስ ጉዳዮችን ወደ ፖለቲካው መድረክ ይዘን መጥተናል ፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በአዲስ መልክ ካስተዋወቅነው ጉዳዮች መሀል አንዱ የዕጩ ምልመላና አቀራረብ ነው፡፡ የምርጫ ወረዳዎችን መሠረት አድርገን የዘረጋነው መዋቅርም ሌላኛው ተጠቃሽ ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በሀገራችን 547 የምርጫ ወረዳዎች አሉን፡፡ እነዚህን የምርጫ ወረዳዎች መሠረት አድርገው የተደራጁ መዋቅሮች ነው ያሉን፡፡ ምርጫ ወረዳዎቹ የራሳቸው ጉባኤ እና ሥራ አስፈጻሚ አላቸው ፡፡ መሪዎቻቸውንም የሚመርጡት ራሳቸው ናቸው፡፡ በአደረጃጀታችን ምርጫ ወረዳዎች የሁሉ ነገር መጀመሪያ ናቸው፡፡

ሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የራሳቸውን ዝግጅት አድርገው የራሳቸውን አስመራጭ ኮሚቴ አስመርጠዋል፡፡ 5 አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴም በየምርጫው ወረዳው ያሉ ለውድድር መቅረብ የሚፈልጉ ዕጩዎችን ሲመዘግቡ ቆይተው ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላም በመስፈርቱ መሠረት አወዳድረው ባለፉት ሁለት ሳምንታት (ከጥር 01 ቀን 2013 ጀምሮ) አብዛኛዎቹ ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን መርጠዋል ፡፡ ዋናው ወድድር ውስጥ ከመገባቱ በፊት በፓርቲው ውስጥ የሚደረግ ፉክክር ተደርጎ፣ በዛ ፉክክር ውስጥ ያለፉ ዕጩዎች ናቸው ወደ ዋናው ውድድር የሚገቡት፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ አዲስ ነገር ነው፡፡ በገዢውም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲው ተሞክሮ አይታወቅም፡፡

ከዚህ ቀደም ዕጩዎች እንዴት እንደሚመረጡ እናውቃለን፡፡ የዕጩ ምዝገባ ጊዜ ሊደርስ ሲል በየቦታው ተሰማርቶ የተገኘውን ዕጩ በማጋበስ ነበር፣ ምልመላ ሲካሄድ የነበረው ወይም ማዕከል ላይ ተቀምጦ አንተ እዚህ ተወዳደር፣ አንቺ እዛ ተወዳደሪ... ተብሎ ነው ምደባ ይካሄድ የነበረው፡፡ አሁንም ድረስ አብዛኞዎቹ ፓርቲዎች ይህንን ሂደት ነው የሚከተሉት፡፡ ኢዜማ ከዚህ የተለየ መንገድ ነው የተከተለው፡፡ ዴሞክራሲን በተግባር መለማመድ አለብን በሚል መርህ ምርጫ ወረዳዎች የራሳቸውን ዕጩዎች መርጠውና ቅድመ ወድድር አድርገው ነው ዕጩዎቻቸውን የመረጡት፡፡

እስካሁን ባለው የዕጩዎች ምርጫ ሂደት በአማራ ክልል ከ138 የምርጫ ወረዳዎች ውስጥ 134 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን መርጠው ወደ ማዕከል ልከዋል፡፡ በደቡብ ክልል ከ123 ምርጫ ወረዳዎች 120 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን መምረጥ ችለዋል ፡፡ በኦሮሚያ ክልል 95 የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን አስመርጠዋል፡፡ ድሬዳዋና ሐረር እያንዳንዳቸው ሁለት የምርጫ ወረዳ ሲሆን ያላቸው አራቱም የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን ማስመረጥ ችለዋል፡፡ ጋምቤላ ሶስት የምርጫ ወረዳዎች ያሉ ሲሆን በሶስቱም የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎች ተመርጠው ተልኮልናል፡፡ አዲስ አበባ ካላት 23 የምርጫ ወረዳዎች በ19ኙ ዕጩዎች ተመርጠዋል፡፡

እስካሁን የጠቀስኩልህ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረቡ የዕጩዎች ዝርዝር ነው፡፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረብነው የዕጩዎች ልክ ለክልል ምክር ቤቶች ዕጩዎቻችንን የምናቀርብ ይሆናል ፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በሀገር አቀፍ ደረጃ በ391 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎችን አስመርጠን አጠናቀናል ፡፡ ከዚህ በኋላ በቀሩት ጊዜያት ኢላማችን የሆነውን 435 ምርጫ ወረዳዎች ላይ በጠቅላላ ዕጩዎችን እናቀርባለን ብለን ነው የምናስበው፡፡

*ዕጩዎችን ለመምረጥ የተከተላችሁት መንገድ ምን ጠቀሜታ አለው?*

የዕጩዎቻችን ምርጫ ኢትዮጵያ ውስጥ እንፈጥራዋለን የምንለውን ድርጅትና እንገነበዋለን የምንለውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሳየት የቻልንበት ሂደት ነው ፡፡ መንግሥት ሳንሆን ራሱ ተፅዕኖ ማሳደር እንደምንችል አሳይተናል፡፡ የእኛን ይህን ተሞክሮ አንዳንዶቹ ነገ ላይ ለመተግበር የሚንደረደሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ እዚህ ሀገር ላይ መንግሥት ሲኮን ብቻ አይደለም ተፅዕኖ ማሳደር የሚቻለው፡፡ የመንግሥትን ሥልጣን ሳይዙ መንግሥት ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ሀገር ላይ አሻራ ማሳረፍ እንደሚቻል በተግባር አሳይተናል ፡፡ እኛ ዕጩዎችን ለመምረጥ የሄድንበት መንገድ ብልፅግናን ጨምሮ ለሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡

*የዕጩዎች መረጣችሁ እርሶ እንደገለፁልኝ አስተማሪ ነው ከተባለ ዕጩዎችን ለመምረጥ የተጠቀማችኋቸውን መስፈርቶች ሊጠቅሱልኝ ይችላሉ?*

በየምርጫ ወረዳው አስመራጭ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ ማዕከሉ ሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የሚገኙ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት የሚገለገሉበት መመዘኛዎችን አዘጋጅቶ ለየምርጫ ወረዳ አስመራጭ ኮሚቴዎች ልኳል፡፡ የትምህርት ደረጃ፣ የፖለቲካ ልምድ፣ ፓርቲው ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ፤ እንዲሁም በማህበረሰብ ወስጥ ያለው ተቀባይነት እና ስነ ምግባር... ሌሎች የተለያዩ መመዘኛዎች አስቀምጠናል፡፡ በተቀመጠው መመዘኛ መሠረት በመመዘን፣ የሚሰጠውን ነጥብ በመስጠት፣ አስመራጭ ኮሚቴው ለወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ ዕጩዎችን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

*በዕጩዎች ምርጫው ላይ ቅሬታ ያላቸው ተወዳዳሪ ዕጩዎች ቅሬታቸው በምን መልክ ይስተናገዳል?*

በአንድ ምርጫ ወረዳ ላይ ብዙ ዕጩዎች ነው የሚቀርቡት፡፡ ለአብነት ብጠቅስልህ 7 ሰው በሚያስፈልግበት የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ ላይ እስከ 35 ሰዎች ያመለከቱበት የምርጫ ወረዳ አለ፡፡ በየምርጫ ወረዳው ላይ በጣም ብዙ ሰዎች ዕጩ ለመሆን አመልክተው ነበር፡፡ ሁሉም ሰው ሊያልፍ አይችልም፡፡ የተወሰነ ሰው ብቻ ነው ሊያልፍ የሚችለው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ቅሬታ አይመጣም ማለት አይቻልም ፡፡ ቅሬታዎች ሊመጡ እንደሚችሉ እንጠብቅ ነበር፡፡ ለዚህም ስንል ቅሬታዎችን የምናስተናግድበት መንገዶች አዘጋጅተን ነበር፡፡

ሥራው ከሰው ጋር የሚሠራ ሥራ እንደመሆኑ መጠን ቅሬታ ሊኖር ይችላል ፡፡ የትኛውም ቅሬታ ያለው አካል በምርጫ ወረዳው ሥር ለሚገኘው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን አይቶ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በምርጫ ወረዳው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ያልረካ አካል ማዕከል ለሚገኘው የብሔራዊ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ማዕከል ላይ የሚገኘው የዲሲፕሊን ኮሚቴ የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጪ አካል ይሆናል፡ ፡ ይህንን መንገድ ተከትለው ቅሬታቸውን እያቀረቡ የሚገኙ አካላት አሉ፡፡

እነዚህ አካላት ቅሬታቸው የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ ቅሬታ ያለው አካል ግን ቅሬታውን በተቀመጠው ቀነ ገደብ ማቅረብ መቻል አለበት፡፡ በየወረዳው ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች የዕጩዎችን ውጤት በዝርዝር በማስቀመጥ በምርጫ ወረዳው ይፋ ያደርጋሉ፡፡ በዛ ላይ ቅሬታ ያለው አካል በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታውን ካቀረበ ቅሬታው የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ ወረዳው ቅሬታዬን አልፈታልኝም ወይም አሰራሩ አላረካኝም ካለም አስቀድሜ እንደገለፅኩልህ ቅሬታውን ማዕከል ለሚገኘው ብሔራዊ የዲሲፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ ቅሬታው በድጋሚ የሚታይበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡

*የቀረቡ ቅሬታዎች ተገቢ ሆነው ከተገኙ ምርጫው የሚደገምበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል?*

አዎ፡፡ ለምሳሌ የምርጫ ወረዳው ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ተቀብሎ ጉባኤው ትክክል አልነበረም፤ ምርጫው መደገም አለበት ብሎ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል ፡፡ እዚህ ውሳኔ ላይ የትኛውም አካል ጣልቃ ሊገባ አይችልም፡፡ የወረዳ ዲሲፕሊን


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

▶ ኮሚቴዎች ጉባኤ በድጋሚ በመጥራት ምርጫ እስከማስደገም የሚደርስ ስልጣን አላቸው፡፡ የወረዳው ዲሲፕሊን ኮሚቴ ባይወስን እንኳ ማዕከል የሚገኘው ብሔራዊ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ጉዳዩን ተመልክቶ ጉባኤ በድጋሚ ጠርቶ፣ ምርጫው በድጋሚ እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡

*ከነገሩኝ በመነሳት ዕጩ ሆነው የቀረቡት ሰዎች የመጨረሻ ዕጩዎች ላይሆኑ የሚችሉበት ዕድል አለ ማለት እችላለሁ?*

አዎ፡፡ ቅሬታ ያላቸው አካላት ግን ምርጫው በተካሄደ በሶስት ቀናት ውስጥ ነው ቅሬታቸውን ማቅረብ ያለባቸው፡፡ በእነዚህ ሶስት ቀናት ውስጥ ቅሬታዎቹ ቀርበው በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ካልሰጠ የተመረጡት ዕጩዎች ሕጋዊ ዕጩዎች ሆነው የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡ እስከዛ ድረስ ግን ዕጩዎቹ ሕጋዊ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ወረዳዎቹ የመጨረሻውን ሪፖርት ወደ ማዕከል ሲልኩ ሶስት ቀናት መጠበቅ አለባቸው፡፡ ሶስት ቀናት ከጠበቁ በኋላ ነው የምርጫውን ሪፖርት ወደ ማዕከል የሚልኩት፡፡ ቅሬታ ያለው አካል ሶስቱን ቀናትን በመጠቀም ቅሬታውን እንዲያቀርብ በሚል ነው ሶስት ቀናት ዘግይተው ሪፖርታቸውን ወደ ማዕከል እንዲልኩ የሚደረገው፡፡ ሰነዶቹ ወደ ማዕከል እየተላኩ ያሉትም በዚህ መልኩ ነው፡፡

*የተከተላችሁት የዕጩዎች ምርጫ ሂደት ብቁ ዕጩዎችን ያወጣልናል ብላቹህ ታስባላችሁ?*

በሂደቱ በጣም ደስተኞች ነን፡፡ ብቃት የትምህርት ዝግጅት፣ የፖለቲካ ተሞክሮ፣ የሥራ ልምድና የሌሎች ድምር ውጤት ነው፡፡ በዚህ መመዘኛ ብቁ ሆነው የተገኙ ዕጩዎች አልፈዋል ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም የምርጫ ወረዳዎች ያደረጉት አንድ ጥሩ ነገር ከእኛ የተሻለ ሰው ከመጣ ያ ሰው ይለፍ ብለው ለመጣው አዲስ ሰው ቅድሚያ ሰጥተዋል፡፡ ይሄ ሀገር የማሻገርና ኢዜማ እንዲያሸንፍ የማድረግ ጉዳይ ነው በማለት መዋቅር ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩና በተለያዩ አገልግሎት ውስጥ የነበሩ ሰዎች፣ የተሻለ ዕጩ በመጣ ወቅት የተሻለ የተባለው ዕጩ እንዲያልፍ ያደረጉበት ሂደት ነው ያለው፡፡ ለዚህ ተግባራቸው ምርጫ ወረዳዎቹ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት ስመጥር የሆኑ ሰዎች አልፈው ስም ዝርዝራቸው ወደ እኛ መጥቷል፡፡ ብቃት ያላቸውና ሀገር መምራት የሚችሉ ዕጩዎች ተገኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡

*በእኔ በኩል ጥያቄዎቼን አገባድጃለሁ፡፡ እርስዎ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ሀሳቦትን ለመሰንዘር መድረኩ ክፍት ነው፡፡*

እዚህ ሀገር ላይ መቶ ምናምነኛ ፓርቲ ለመሆን አይደለም ፓርቲ የመሰረትነው፡፡ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል ድርጅት መፍጠርን አላማ አድርገን ነው የተነሳነው፡፡ ዴሞክራሲንም ከራሳችን ቤት በመነሳት ነው የምንገነባው በማለት ነው ቃል የገባነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ችለናል ማለት ይቻላል፡፡

ባለፉት ሁለት ሳምንታት በየወረዳው ያካሄድናቸውን የዕጩዎች ምርጫ ብትመለከት ስናልመው የነበረውን ህልም የኖርንበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ራስን ዕጩ አድርጎ ለማቅረብ የነበረው ሰላማዊ ፉክክር ስትመለከት ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይሆናል ተብሎ ያልታሰበ ነው፡፡ በተቃዋሚውም ሆነ በገዢው ፓርቲ ከዚህ ቀደም የነበረውን የዕጩ አመራረጥ በመቀየርና አዲስ የዕጩ አመራረጥ ማስተዋወቅ ችለናል፡፡ ኢዜማም ከዚህ በኋላ በዕጩ አቀራረብ ሂደት ውስጥ ወደ ኋላ አይመለስም፡፡ ይህንኑ አጠናክረን ነው ወደፊት የምንሄደው እንጂ ወደኋላ አንመለስም፡፡ አቅም ያላቸው ሌሎች ፓርቲዎችም ከዚህ በኋላ ይህን መንገድ ይከተላሉ ብለን ነው የምናምነው፡፡

የዕጩ አመራረጣችን የመንግሥትን ሥልጣን ሳንይዝ ተፅዕኖ ያሳደርንበት አንዱ ሂደት ነው፡፡ ይህ ለእኛ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ላለፉት አንድ ዓመት ከስድስት ወራት ሲሰራ የነበረው መዋቅር በተግባር የተፈተነበትና በተግባርም ራሱን ያስመሰከረበት ነው፡፡ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በተለያዩ ክልሎች ይህን ሁሉ ዕጩ ማዘጋጀት መቻልና በጉባኤ ማስመረጥ መቻል መዋቅሩ በተግባር ምን ያህል እንደሚንቀሳቀስ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ሥራ ውስጥ ሲሳተፉ የነበሩ አካላት በጠቅላላ ምስጋና የሚገባቸው ናቸው፡፡ ሂደቱ ለሀገር የምንችለውን ያዋጣንበት ተግባራዊ እርምጃ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ያለው ሥራ የተመረጡትን ዕጩዎች በምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማስመዝገብ ነው የሚሆነው፡፡ ሁሉም ዕጩዎች በየምርጫ ወረዳዎቻቸው ሄደው የሚመዘገቡበትን ሂደት ከየካቲት 08 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ይኖራል፡፡ የዕጩ ሂደቱ በዘመቻ መልኩ እንደተሰራው ሁላ የምርጫ ዘመቻው በከፍተኛ ሁኔታ የምንንቀሳቀስበት ይሆናል፡፡ አሁን ላይ አዳዲስ አሻራዎቻችንን እንዳሳራፍነው ሁሉ የምርጫ ዘመቻው አዳዲስ አሻራዎቻችንን የምናሳይበት መሆን አለበት፡፡ ፉክክራችን ከማንም ጋር ሳይሆን ራሳችን ካስቀመጥነው መርህ ጋር ነው፡፡ ከ40 በላይ የፖሊሲ ሰነዶችን መቅረፅ መቻላችን፣ በ435 የምርጫ ወረዳዎች ላይ መዋቅር መዘርጋታችን እንዲሁም ዕጩዎቻችንን ለመምረጥ የሄድንበትን መንገድ ስትመለከት የመረጥነው መንገድ በየትኛውም ፓርቲ ሊደረግ የሚችል አይደለም፡፡

አንዳንዶቹ ፖሊሲዎቻችን በመንግሥት ደረጃ ጭምር ያልታሰበባቸውና ያልተቀረፁ ፖሊሲዎች ናቸው፡፡ ይህንን ሁላ ያደረግነው ለይስሙላ ብለን አይደለም፡፡ የመረጥነው መንገድ ረጅምና አድካሚ ነው፡፡ ለሌሎች ፓርቲዎችም አስተማሪ መሆን አለበት ብለን ስላመንን ነው ይህንን ረጅምና አድካሚ መንገድ መከተል ምርጫችን ያደረግነው፡፡ በዚህም ሁሉም የኢዜማ አባላት ሊኮሩ ይገባል፡፡ የሚቀጥሉት ሶስት ወራት ደግሞ ወሳኙን ሥራ የምንሰራበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ሁሉም የኢዜማ አባላት ዝግጁ እንዲሆኑ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

*ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቹ ስም አመሰግናለሁ፡፡*

እኔም ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ፡፡





# በአዲስ አበባ በመሬት ወረራ እና ሕገ ወጥ ቤት እደላ ላይ የተሳተፉ አመራሮች በሕግ ሊጠየቁ ይገባል !

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ወረራና በጋራ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ ጥር 18 ቀን 2013 ዓ.ም ይፋ ያደረገው ጥናት መሠረታዊ ችግር ያለበት ነው ሲሉ የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ዳንኤል ሺበሺ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ500 ካሬ ሜትር ይዞታ በላይ ያለ መሬትን ብቻ ወረራ ተካሄዶበታል ወይ ብሎ ጥናት ማካሄዱን የጠቀሱት ዳንኤል ሺበሺ፣ ሌሎች ይዞታዎችስ ለምን አልተጠኑም? ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ‹‹70 ካሬና 140 ካሬ መሬት ሲሰጥ አልነበረም እንዴ? ጥናቱ ከ500 ካሬ ሜትር በታች ያሉ ይዞታዎች ላይ መሬት ወረራ ተካሄዷል ወይ? የሚለውን አለማጥናቱ የጥናቱ መሠረታዊ ችግር ነው›› በማለት የጥናቱን ክፍተት ጠቁመዋል፡፡

ኢዜማ በመሬት ወረራና በጋራ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ አጥንቶት የነበረው ጥናት ከተማ አስተዳደሩ ጥናቱን ሲያካሄድ እንደተመለከተው የገለፀ ሲሆን፣ ኢዜማ ተወረረ ካለው መሬት ውስጥም 2/3ኛው በውሃና ፍሳሽ መሥሪያ ቤት የተያዘ እንጂ መሬት ወረራ ያልተካሄደበት እንደነበር ምክትል ከንቲባ አዳነች አበቤ ገልፀዋል፡፡ ይህንን በማስመልከት ዜጎች መድረክ፣ ኢዜማ ጥናቱን ሲያካሄድ የጥናት ቡድኑ አባል ለሆኑት ዳንኤል ሺበሺ፣ ጥያቄ ያነሳች ሲሆን ፓርቲያቸው በቦታ፣ በመንደር ስም፣ በካርታ ቁጥር ለይቶ ተወረረ ያለውን መሬት ይፋ ማድረጉን አስታውሰው፣ የፅሁፍ፣ የቪዲዮና የሰው ማስረጃ በጥናት ውጤታቸው አካተው ይፋ ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

‹‹መሬት ተወረረ ብለን በዘፈቀደ አንንቀሳቀስም›› ያሉት ዳንኤል፣ መሬቱን ያጠረው አካል ማንነው? መቼነው የታጠረው? እንዴት ነው የታጠረው? የሚለውን በደንብ አጣርተው የጥናት ውጤታቸውን ይፋ ማድረጋቸውን አስታውሰዋል፡፡ ፓርቲያቸው ጥናቱን ሲያካሄድ ታጥረው ያያቸው በርካታ ቦታዎች እንደነበሩና በጥናት ውጤቱ ግን እንዳላካተታቸው ጠቁመዋል፡፡

‹‹ታጥሮ ያየነውን ቦታ በጠቅላላ የተወረረ መሬት ነው ብለን አልወሰድንም፡፡ ለልማት የታጠሩ ቦታዎች አሉ፤ ይታወቃሉም፡፡ ተገቢውን ማጣራት ካደረግን በኋላ የተውናቸው ቦታዎች አሉ፡፡ 2/3ኛው ቦታ በውሃና ፍሳሽ የተያዘ ነው ብለዋል፡፡ እኛ እንዴት በውሃና ፍሳሽ የተያዘን ቦታ መሬት ወረራ ተካሄዶበታል ልንል እንችላለን?! ይህ ፍፁም ሀሰት ነው፡፡ እንዲህ ያለ ፍረጃ፣ ከንቲባዋንም ሆነ የሚመሩትን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን የሚመጥን አይደለም፡፡ በትላንትናው መንገድ እያወናበድን እንሄዳለን ካላሉ በስተቀር የተከተሉት መንገድ አዋጭ አይደለም፡፡ በጥናት ውጤታችን ተወሯል ብለን ካካተትናቸው መሬት ውስጥ ውሃና ፍሳሽ ያጠረውን ቦታ አንድም ቦታ አላካተትንም፡፡ ይህ ፍፁም ሀሰት ነው›› በማለት ለዜጎች መድረክ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ኢዜማ ጥናቱን እንዲያካሄድ ያዋቀረው ኮሚቴ የመሬት ወረራ የተካሄደባቸውን አካባቢዎች በአካል ቅኝት በማድረግ ከመስክ ምልከታ የሚገኙ ማስረጃዎችን በፎቶ እና በቪዲዮ አስደግፎ የሰበሰበ ሲሆን እንዲሁም ከተለያዩ አካላት በጥቆማ መልክ የደረሱንን የካርታ ምስሎች እና የዲጂታል እቅጣጫ መጠቆሚያ ነጥቦች ለማረጋገጥ እና ተጨማሪ መረጃዎችን ▶

ለመሰብሰብ ሙከራ አድርጓል፡፡ ይህም በጥናቱ ውጤት ላይ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ወደ 25 የሚጠጉ የተመረጡ በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚገኙ የመሬት ወረራ የተካሄደባቸው እና 5 የተመረጡ ኢፍትሀዊ አሰጣጥ የተፈጸመባቸው የኮንዶሚኒየም ሳይቶች የመስክ ምልከታ ተካሂዶ ሁሉም የመስክ ምልከታዎች መስክ ምልከታ መምሪያ ቅጽ በመጠቀም መመዝገባቸውንም በጥናቱ ሪፖርት ላይ ተጠቅሷል፡፡

የመሬት ወረራና ኢ-ፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕደላ በማስመልከት ኢዜማ ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ይፋ ያደረገውን ጥናት ለመገናኛ ብዙኃንና ለሕዝብ ይፋ ከማድረጉ በፊት የከተማ አስተዳደሩ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ እንዲሰጡ ጥያቄ ቀርቦለት የነበረ ቢሆንም ምንም ዓይነት መረጃ ከመስጠት የተቆጠበ መሆኑንና ጥናቱ ከተካሄደ በኋላም በጥናቱ ላይ ምላሻቸውን እንዲሰጡ ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ ምላሽ ሳይሰጡ እንደቀሩ ዳንኤል ሺበሺ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

‹‹ምላሽ ሊሰጡን ይቅርና በጽህፈት ቤታችን በጉዳዩ ላይ ያዘጋጀነውን የፓናል ውይይትም እንዳናካሄድ ክልከላ አድርገውብናል፡፡ መግለጫ እንዳንሰጥም አግደውናል›› በማለት የከተማ አስተዳደሩን ድርጊቶች አስታውሰዋል፡፡

ኢዜማ ጥናቱን ሲያካሄድ ከገጠሙት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ እና ዋነኛው በየትኛውም መዋቅር ላይ ያሉ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ማስታወቁ የሚታወስ ነው፡፡ ማብራሪያ እንዲሰጡበት በደብዳቤ እንዲሁም አንዳንዶቹ ጋር በአካል በመገኘት ተደጋጋሚ ሙከራ ቢደረግም ቢሯቸውን ለንግግር ዝግ ማድረጋቸውንና ማብራሪያ ከተጠየቁ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሀል በዋነኝነት የሚጠቀሰው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት የተጻፈለትን ደብዳቤ ቢቀበልም፣ በደብዳቤም ምላሽ ለመስጠትም ይሁን በአካል በመቅረብ ለማነጋገር የተደረገው ጥረት ተቀባይነት ሳያገኝ እንደቀረ ኢዜማ የጥናቱን ግኝት ይፋ ባደረገበት ሪፖርት ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡

የፌደራል ዕንባ ጠባቂ ተቋም ኢዜማ ያወጣውን የጥናት ሪፖርት መሠረት አድርጎ የችግሩን ሁኔታ ለማጣራት የቤቶች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጁን ለማነጋገርና መልስ ለማግኘት ቢጠይቅም፣ ምንም ዓይነት መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ዋና ዕንባ ጠባቂ እንዳለ ኃይሌ መግለፃቸው የሚታወስ ነው፡፡

ምክትል ከንቲባዋ አዳነች አቤቤ፣ ከተማ አስተዳድሩ ባደረገው ጥናት ከ1997 ዓ.ም እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉ ዓመታት የተካሄዱ የመሬት ወረራዎችን ማጥናታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከለውጡ ወዲህ በብዛት መሬት ተወሯል ተብሎ የሚገለፀውን ወሬም ‹‹ከለውጡ ወዲህ ነው በስፋት የመሬት ወረራው የተካሄደው የሚባለው ፍፁም ከእውነት የራቀ ነው›› ሲሉ አስተባብለዋል፡፡ አብዛኛው የመሬት ወረራዎች ከለውጡ በፊት ሲካሄዱ እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡

ይህንን የእሳቸውን አስተያየት ተከትሎ ከዜጎች መድረክ ጥያቄ የተነሳላቸው ዳንኤል ሺበሺ፣ ይህንን አስተያየት ለመቀበል እንደሚቸግራቸው ገልፀዋል፡፡

‹‹የመሬት ወረራው ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለ ችግር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገው የመሬት ወረራው አሁን የተጀመረ እንዳልሆነ ለማሳየት የተጠቀሙት የፖለቲካ ጨዋታ ነው፡፡ ይህን እኛ አንቀበልም›› በማለት ምላሻቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በኢዜማ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የኮሚኒኬሽን ክፍል ኃላፊ የሆኑት ዘላለም ወርቅአገኘሁ፣ በበኩላቸው ፓርቲያቸው ጥናቱን ያካሄደው ለውጡ ከመጣ በኋላ የተፈፀሙ የመሬት ወረራዎችን መሆኑን አስታውሰው፤ ከንቲባዋ፣ ኢዜማ የመሬት ወረራ ተካሄዶበታል ካለው ቦታ ውስጥ 2/3ኛውን አንቀበለውም ቢሉም 1/3ኛው የሚሆነው ግን እንደሚቀበሉትና በሕገ ወጥ መንገድ ተወሮ የታጠረ መሆኑን ማረጋገጣቸውን ጠቅሰው፣ 1/3ኛውን እንደሚቀበሉት ሲጠቅሱ ከለውጡ ወዲህ የመሬት ወረራ መካሄዱን አምነዋል። ለዚህም ተጠያቂ የሚሆን አመራር ሊኖር እንደሚገባ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡

ምክትል ከንቲባዋ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በሚመለከትም 22915 ቤቶች ለአርሶ አደሮች በካቢኔ ውሳኔ መተላለፉን ገልፀዋል፡፡ ኢዜማ ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ባወጣው ጥናት ላይ ከጋራ መኖሪያ ቤት ጋር በተገናኘ በግልፅ የታየ የመንግሥት ሕገ ወጥ ተግባር መፈፀሙን መግለፁ ይታወሳል፡፡ ‹‹ኢ-ፍትሐዊ ሕጎችን እና መመሪያዎችን በማውጣት እና ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሕጎችን እና ደንቦችን በማሻሻል ለካቢኔው እና ለከንቲባው በተሰጠ ልዩ ሥልጣን (መመሪያ ቁጥር 1 እና 2/2011፣ ክፍል 2 አንቀጽ 12/2) ከንቲባውም ሆነ ካቢኔያቸው ቤቶችን እንደፈለጉ እንዲያድሉ ምክንያት ሆኗል። በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢፍትሐዊ በሆነ መልኩ ፈጽሞ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ለማይገባቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ቤት የማስተላለፍ ተግባር እንደፈፀመና እየፈጸመ መሆኑን አረጋግጠናል›› ሲል በጥናቱ ላይ ይፋ ማድረጉ አይዘነጋም፡፡

ለውጡን ተከትሎ የመሬት ወረራው ተጠናክሮ መቀጠሉን የጥናቱ ግኝቶቹን ይፋ ባደረገበት ሪፖርት የገለፀው ኢዜማ፣ ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ ተግባር በኢትዮጵያ አዲስ ያልሆነ እና በተለያዩ ጊዜዎች እና አካባቢዎች ትልቅ ችግር ሆኖ የቆየ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ ግን በዚህ ደረጃ እና ፍጥነት የተስፋፋበት ጊዜ እንዳልነበር መጥቀሱ የሚታወስ ነው፡፡

ኢዜማ ጥናቱን ባካሄደባቸው አምስት ክፍለ ከተሞች ላይ ባጠቃላይ 213ሺህ 9መቶ ካ.ሜ የሚሆን መሬት በወረራ መያዙን ማረጋገጡ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ የጥናቱን ሪፖርትም ለፌደራል ፖሊስ፣ ለጠቅላይ አቃቤ ሕግ እና ለፌደራል ሥነምግባር እና ፀረሙስና ኮሚሽን መላኩ አይዘነጋም፡፡ እስካሁን ድረስ ከመሬት ወረራም ሆነ ከኢፍትሐዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕደላ ጋር በተያያዘ የትኛውም አካል ተጠያቂ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡





# ኢዜማ በ391 ምርጫ ወረዳዎች ላይ ዕጩዎቹን አስመረጠ

## በቀሩት የምርጫ ወረዳዎች ላይ በያዝነው ሳምንት ዕጩዎችን የሚያስመርጥ ይሆናል

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በምርጫ 2013 የሚያቀርባቸውን ዕጩዎች በየምርጫ ወረዳዎቹ እያስመረጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ፓርቲው የዕጩዎቹን ምርጫዎች ለማገባደድ እየተቃረበ መሆኑን ዜጎች መድረክ ከድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የደረሳት መረጃ ያስረዳል ፡፡

ኢዜማ እስካሁን ባለው የዕጩዎች ምርጫ ሂደት በአማራ ክልል ከ138 የምርጫ ወረዳዎች ውስጥ 134 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎችን ያስመረጠ ሲሆን፣ በደቡብ ክልል ከ123 ምርጫ ወረዳዎች 120 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን መምረጥ ችለዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል 95 የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን ሲመርጡ በድሬዳዋና ሐረር የሚገኙ አራቱም የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎቻቸውን ማስመረጥ ችለዋል፡፡ በጋምቤላም ሶስት የምርጫ ወረዳዎች ያሉ ሲሆን በሶስቱም የምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎች መመረጥ ችለዋል፡፡ አዲስ አበባ ካላት 23 የምርጫ ወረዳዎች በ19ኙ ዕጩዎች መመረጣቸውን ከድርጅት ጉዳይ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በሀገር አቀፍ ደረጃ በ391 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎች መመረጥ መቻሉን የደረሰን መረጃ ያስረዳል፡፡

በተካሄደው የዕጩዎች ምርጫ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን በምን መልክ ማቅረብ እንደሚችል ለኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ዜጎች መድረክ ጥያቄ አንስታ የነበረ ሲሆን፣ ሥራው ከሰው ጋር የሚሠራ ሥራ እንደመሆኑ መጠን ቅሬታ ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰው፣ የትኛውም ቅሬታ ያለው አካል በምርጫ ወረዳው ሥር ለሚገኘው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ ‹‹የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን አይቶ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል›› ያሉት ኃላፊው በምርጫ ወረዳው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ያልረካ አካል ማዕከል ለሚገኘው የብሔራዊ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ጠቅሰዋል፡፡ ማዕከል ላይ የሚገኘው የዲሲፕሊን ኮሚቴ የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጪ አካል መሆኑን ያወሱት ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ይህንን መንገድ ተከትለው ቅሬታቸውን እያቀረቡ የሚገኙ አካላት እንዳሉም አስረድተዋል፡፡

ቅሬታቸውን ያቀረቡ አካላት ቅሬታቸው የሚስተናገድ መሆኑን የጠቀሱት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ቅሬታ ያለው አካል ግን ቅሬታውን በተቀመጠው ቀነ ገደብ ማቅረብ መቻል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ በየወረዳው ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች የዕጩዎችን ውጤት በዝርዝር በማስቀመጥ በምርጫ ወረዳው ይፋ እንደሚያደርጉ ያስታወሱት ኃላፊው፣ በዛ ላይ ቅሬታ ያለው አካል በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታውን ካቀረበ ቅሬታው የሚስተናገድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ወረዳው ቅሬታውን አልፈታልኝም ወይም አሰራሩ አላረካኝም ካለም ማዕከል ለሚገኘው ብሔራዊ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን በማቅረብ ቅሬታው በድጋሚ የሚታይበት አሰራር መዘርጋቱን ተናግረዋል፡፡

ኢዜማ፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የዕጩዎች ልክ ለክልል ምክር ቤቶች ዕጩዎችን የሚያቀርብ ሲሆን በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በሀገር አቀፍ ደረጃ በ391 ምርጫ ወረዳዎች ዕጩዎችን ተመርጠው የተጠናቀቁ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ በቀሩት ጊዜያት ፓርቲው ኢላማ አድርጎ ያስቀመጠውን 435 ምርጫ ወረዳዎች ላይ በጠቅላላ ዕጩዎችን ያቀርባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

# ኢዜማ፣ ለምርጫ አስፈፃሚነት ከተመለመሉት ሰዎች መሀከል ጥያቄ ያነሳባቸውን ለምርጫ ቦርድ አመለከተ

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈፃሚነት የመለመላቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኛ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን ለማጣራት ለሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች የአስፈፃሚዎቹን ስም ዝርዝር በመላክ ማጣራት እያካሄደ ነው:: ቦርዱ አስፈጻሚዎችን ከመለመለ በኋላ የተመለመሉትን አስፈጻሚዎች ስም ዝርዝር ለፖለቲካ ፓርቲዎች በመላክ ፓርቲዎች ገለልተኝነታቸው ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እንደሚያደርግ መናገሩ የሚታወስ ነው:: በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ዙር ወደ 750 ምርጫ አስፈጻሚዎች ስም ዝርዝር ኢዜማ ደርሶታል::

የተላኩላቸውን ምርጫ አስፈጻሚዎች የፓርቲውን መዋቅር በመጠቀም ገለልተኝነታቸውን ለማጣራት ሙከራ እንዳደረጉ ለዜጎች መድረክ የገለፁት የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ዜጎች መድረክ ከዚህ ቀደም የምርጫ አስፈፃሚዎቹን ስም ዝርዝር ይዞ ለማጣራት አቅም አላችሁ ወይ ብላ ጥያቄ አንስታላቸው እንደነበር አስታውሰው፤ የፓርቲውን መዋቅር በመጠቀም ምርጫ ቦርድ የመለመላቸውን ምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነት ማጣራት መቻላቸውንተናግረዋል::በማጣራትሂደቱም አንዳንዶቹ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከዚህ ቀደም የኢሕአዴግ አባል የነበሩ አሁን ደግሞ የብልፅግና አባል መሆኑን እንደደረሱበትና ይህንንም በማስረጃ በማስደገፍ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መላካቸውን ለዜጎች መድረክ አስታውቀዋል::

‹‹የእኛ መዋቅሮችም የብልፅግና አባል የሆኑትን ሰዎች አጣርተው ከእነ ስም ዝርዝራቸውና ከመቼ ጀምሮ የብልፅግና አባል እንደሆነ ጠቅሰው ስማቸውን ልከውልናል:: አንዳንዶቹ ሰዎች ለብልፅግና ፓርቲ የአባልነት መዋጮ የከፈሉበትን ደረሰኝ ጭምር አያይዘው ልከውልናል:: ይህንንም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገቢ አድርገናል›› ብለዋል::

ምርጫ ቦርድ በሁለተኛ ዙር የሌሎች ሰዎችን ስም ዝርዝር የላከላቸው መሆኑን የጠቀሱት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ይህንንም የሚያጣሩ መሆናቸውንና ተገቢውን ማጣራት ካደረጉ በኋላ ለቦርዱ ምላሻቸውን እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል::

አንዳንድ ቦታዎች ላይ በምርጫ አስፈጻሚነት እየተሳተፉ ያሉ ሰዎች በግልፅ ወገንተኝነት የታየባቸው ናቸው ያሉት ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ዋናው የአስፈጻሚነት ሚና ገለልተኝነት መሆኑን ጠቅሰው፤ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ገለልተኝነትን በጥንቃቄ ሊመረምረው ይገባል ብለዋል:: ቦርዱ፣ ፓርቲያቸው የገለልተኝነት ጥያቄ ያነሳባቸውን ሰዎች ዝርዝር በመመልከት ሌሎቹ አስፈጻሚዎች እንዴት ነው የተመለመሉት የሚለውን ያጣራል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል:: ብሔራዊምርጫቦርድ፣ለምርጫአስፈጻሚነት የመለመላቸውንና ገለልተኝነታቸው ላይ ጥያቄ ያነሳንባቸውን እነዚህን ሰዎች በሌሎች ሰዎች ይቀይራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፤ መቀየርም ይኖርበታል ብለዋል ዋሲሁን ተስፋዬ::

ኢዜማ በገለልተኝነታቸው ላይ ጥያቄ ያነሳባቸውና ስም ዝርዝራቸው ለምርጫ ቦርድ የተላከው የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ሲፈርሙባቸው የነበሩ የደሞዝ መክፈያ ሰነድና የብልፅግና አባል መሆናቸውን የሚያሳይ የአባልነት መዋጮ የከፈሉበት ደረሰኝ በማያያዝ ለምርጫ ቦርድ ገቢ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል::

ሰነድ ማስረጃ ያልተገኘባቸው ደግሞ የሰው ማስረጃ በማቅረብ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጥር 19 ቀን 2013 ዓ.ም በደብዳቤ እንዲደርሰው መደረጉን ዜጎች መድረክ መረዳት ችላለች::

ኢዜማ፣ በመንግሥት ሥር ያሉ እንደ ሥራ ፈጠራ ኮሚሽን ዓይነት ተቋማት፣ ምርጫ አስፈጻሚ መሆን የምትፈልጉ ሰዎች መመዝገብ ትችላላችሁ የሚል ማስታወቂያ ለጥፎ ምልመላ ሲያካሄዱ ደርሶበት ይህንን ከእነ ሰነድ ማስረጃው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቅረብ፣ ከቦርዱ ውጪ የትኛውም አካል ምርጫ አስፈፃሚዎችን የመመልመል ስልጣን እንደሌለው ማስታወቁ አይዘነጋም::





# ‹‹በጋምቤላ ክልል የሚገኙ የኢዜማ አባላት ያለፈቃዳቸው ከደሞዛቸው ለብልፅግና ፓርቲ 4 በመቶ ተቆርጦ እየተከፈለ ይገኛል››

## የኢዜማ የጋምቤላ ክልል የምርጫ ዞን አስተባባሪ (ኦኬሎ አኳይ)

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



ፎቶ ከፋይል

በጋምቤላ ክልል የሚገኙ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አባላት ለብልፅግና በግዴታ መዋጮ እንዲከፍሉ እየተገደዱ መሆኑ ተገለጸ::

የኢዜማ አባላት ያለፈቃዳቸው ለብልፅግና ፓርቲ መዋጮ እንዲያዋጡ እየተደረገ እንዳለና ለብልፅግና ፓርቲ መዋጮ አንከፍልም የሚሉት ላይ በሥራቸውም ሆነ በማኅበራዊ ህይወታቸው ከፍተኛ ተፅዕኖ እየተደረገባቸው እንዳለ የገለጹት የኢዜማ የጋምቤላ ክልል የምርጫ ዞን አስተባባሪ ኦኬሎ አኳይ፣ የመንግሥት ሥራ እየሰሩ የሚገኙ የኢዜማ አባላት ያለፈቃዳቸው ከደሞዛቸው ለብልፅግና ፓርቲ ተብሎ 4 በመቶ እንደሚቆረጥባቸው ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል::

ኢዜማ በክልሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለማስመረጥ ዝግጅት ሲያደርግ የዞኑና የወረዳው አመራሮች ‹‹እናንተ አባላት የላችሁም›› በማለት መሰብሰቢያ አዳራሽ ክልከላ እንደሚደረግባቸው፣ የኢዜማ አባላት በአካል ሲቀርቡም እነዚህ ለእኛ መዋጮ እየከፈሉ ነው:: የእናንተ አባል አይደሉም በማለት የመሰብሰቢያ አዳራሽ እንደማይፈቅዱ፣ አዳራሹን በብዙ ውትወታ ማግኘት ቢቻል እንኳን የአዳራሹ ቁልፍ እንዳይገኝ በማድረግ ለሌላም ሰው የአዳራሽ ፈቃድ በመስጠት ሆን ብለው ኢዜማን ከሕዝቡ ጋር ለማጋጨት ይሰራሉ በማለት በመንግሥት አካላት በኩል እየደረሰብን ይገኛል ያሉትን ጫና አስተባባሪው ለዜጎች መድረክ አስረድተዋል::

‹‹ኢዜማ የፌዴራል ሥርዓቱን ንዶ የድሮ ሥርዓት መልሶ ሊያመጣ ነው›› የሚል ቅስቀሳ እየተደረገባቸው እንደሚገኝ የገለፁት ኦኬሎ አኳይ፣ የጉደሬ እና የክልሉ አመራሮች የኢዜማ አባላትን ስም ዝርዝር እንዲያመጡ ቢያስገድዱም፣ ስም ዝርዝር መስጠት የሚገባን ለሚመለከተው አካል እንጂ ለእናንተ አንሰጣችሁም ብለው ምላሽ መስጠታቸው ገልፀዋል::

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በጋምቤላ ክልል የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አፋጣኝ ትኩረት እንደሚሻ፣ የእስረኞችን አያያዝ ማሻሻል እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት ሊረጋገጥ ይገባል በማለት ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠ ሲሆን፣ በክልሉ የሚኖሩ 90 ሰዎች በክልሉ ፖሊስ ቁጥጥር ስር ቢውሉም፣ በፌዴራል ፖሊስም ሆነ በክልሉ ፖሊስ በኩል የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ሂደት አለመኖሩ እንዲሁም የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ቤተሰብ በመሆናቸው ከመንግሥት ሥራ የታገዱ እና ያለፈቃዳቸው 'ለብልጽግና ፓርቲ መዋጮ' በሚል ከደሞዛቸው ላይ የመዋጮ ክፍያ የተቆረጠባቸው ሰዎች መኖራቸውን መግለጹ ይታወቃል::

# በጅግጅጋ የሚገኙ የኢዜማ አባላቶች ላይ ተፅዕኖ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ ተገለፀ

ጥር 20 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በጅግጅጋ የሚገኙ አባላቶቹ ላይ ተፅዕኖ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ የጅግጅጋ ምርጫ ወረዳ የኢዜማ ሊቀመንበር ገብረማርያም ቦቄ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ኢዜማ ከምሥረታቸው ጀምሮ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል እንደሚያደርገው በጅግጅጋም አባላትን በመመልመልና በማደራጀት ለሥራ ማስፈጸሚያ የሚሆን ቢሮ ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ ቢገኝም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባልተለመደ መልኩ በጅግጅጋ በአባላቱ ላይ ጫና እየተደረገባቸው ከሥራ ገበታቸውም የመፈናቀል አደጋ እንደተጋረጠባቸው የገለፁት የኢዜማ የጅግጅጋ ወረዳ ሊቀ መንበር ገብረ ማርያም ቦቄ፣ ለረዥም ዓመታት ካስተማሩበት ትምህርት ቤት ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መባረራቸውን ለዜጎች መድረክ አስታውቀዋል፡፡

በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት በመላ ሀገሪቱ ትምህርት ከተዘጋ በኋላ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በጅግጅጋ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ገበታ መመለስ ዙሪያ ላይ በተነሳ ውይይት፣ መምህራኖቹ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ኃላፊዎቹ ጥያቄውን በሌላ መልክ እንዲታይ በማድረግ፣ የኢዜማ የጅግጅጋ ወረዳው ሊቀመንበር ጨምሮ 37 መምህራን በ10 ቀናት ውስጥ ጡረታ ውጡ በማለት ከሥራ ገበታቸው እንዲሰናበቱ መደረጋቸውን ገብረ ማርያም ቦቄ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በፊት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በክልሉ የሚገኘው የመንግሥት ታችኛው መዋቅር ዘርፈ ብዙ ችግር መኖሩን የኢዜማ አመራሮች ቢያሳውቁም፣ ችግሮቹ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመሩ እንደመጡና በታችኛው የመንግሥት መዋቅር ተመሳሳይ ድርጊትና ጫና እንዳለ ገብረ ማርያም ቦቄ አስረድተዋል ፡፡